# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 95 መጋቢት 2 2002 ዓ.ም


ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## ጀኖሳይድ ወች የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት ለፍርድ እንዲቀርቡ በድጋሜ አሳሰበ

የድርጅቱ ፕሬዚዳንት የሆኑት ዶ/ር ግሪገሪ ስታንተን ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ለሆኑት ለዳኛ ናቫንቴም ፒለይ በጻፉት ደብዳቤ "ከዲሰምበር 13 እስከ ዲሰምበር 16 ፣2003 ዓም በተደረገው ጭፍጨፋ ለተገደሉት 424 አኙዋኮች ተጠያቂ የሆኑ ሰዎች እስከዛሬ ድረስ ለፍርድ አለመቅረባቸውን ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንቱ በደብዳቤያቸው "በ2004 ዓም በተመሳሳይ መልኩ ለተገደሉት ከ1ሺ በላይ አኙዋኮችም ተጠያቂ የሆኑ ሰዎች እስከዛሬ ለፍርድ አልቀረቡም። በ2004 ዓም ጀኖሳይድ ወች ባደረገው ማጣራት የኢትዮጵያ መንግስት አቅዶ በርካታ አኙዋኮችን መግደሉንና ግድያውን ለመሸፋፈን ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን ጠቅሷል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግሰት በኢትዮጵያና በሶማሊያ በርካታ ተመሰሳሳይ ወንጀሎችን ፈጽሞአል። በኦጋዴንም እንዲሁ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሞአል። ይህን የፈጸሙ ሰዎችን በዝምታ የማለፍ ባህል እየተስፋፋ ነው" ሲሉ ገልጸዋል።

አሁን የቀረበው ደብዳቤ ጀኖሳይድ ወች በማርች 2009 ዓም ለ ተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኮሚሽነር ለጻፈው ድብዳቤ ቀጣይ ክፍል ሲሆን፣ በመጀመሪያው ደብዳቤ ድርጂቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጸመ ያለውን ወንጀል የተባበሩት መንግስታት ድርጂት እንዲያጣራ ጠይቆ እንደነበር ይታወሳል። እስከዛሬ ድረስ ግን ለጥያቄያው መልስ እንዳላገኘ ጄኖሳይድ ወች አስታውቋል። ዶ/ር ስታንተን በደብዳቤያቸው "በተለይ ረሀብንና ምግብ መከልከልን እንደ መሳሪያ በመጠቀም የኦጋዴንን ህዝብ ለመጉዳት የሚደረገው እርምጃ በእጅጉ እንዳሳሰባቸው፣ አካባቢውን ከመከላከያ ሰራዊት በስተቀር ሌላ አካል እንዳይጎበኘው መደረጉ ትልቅ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን" ገልጸዋል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## እርዳታን ለፖለቲካ ስራ ማዋል የወያኔ የተለመደ ተግባርና መለያ ባህሪውም መሆኑን ግንቦት 7 አስታወቀ

የካቲት ሃያ አራት ቀን 2002 ዓም ታዋቂው ዓለማቀፍ የዜና አውታር ቢቢሲ የወያኔው አገዛዝ ከ1977 እስከ 1978 ዓም ባለው ጊዜ በወቅቱ በርሃብ እንደቅጠል ይረግፉ ለነበሩ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ህይወት መታደጊያ ይሆን ዘንድ ከተለያዩ ለጋሽ አካላት የተቀበለውን በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ለጦር መሳሪያ ግዢ ያዋለው መሆኑን ማረግገጡን ይፋ ማድረጉን ተከትሎ የግንቦት 7 ንቅናቄ በድረ ገጹ ላይ መግለጫ አውጥቷል። ግንቦት ሰባት ባወጣው በዚሁ መግለጫ ምንም እንኳን ይህን አይን ያወጣ የውንብድና ተግባር ወያኔ ከፈጸመው ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላ ቢቢሲ እስከዛሬ ለምን እንዳቆየው ግልጽ ባይሆንም፣ የቢቢሲ ዜና እወጃ ቢዘገይም መመስገን ያለበት ጉዳይ መሆኑን አስታውቋል።

በመቀጠልም ከወያኔ የቀድሞ አመራር አካላት ውስጥ የወያኔ ጦር አዲስ አበባን ሲቆጣጠር በጦር አዛዥነት የመሩት አቶ ስየ አብርሃ፤ የገንዘብና ሂሳብ ዋና ተቆጣጣሪ የነበሩት አቶ ገብረመድህን አርአያ፤ እንዲሁም የወያኔ መስራቺ አባልና ከፍተኛ አመራር አቶ አረጋዊ በርሄ የቢቢሲን ዘገባ የተቀበሉና ያረጋገጡት ሲሆን አቶ ገብረ መድህን አርአያና አቶ አረጋዊ በርሄ በሰጡት የምስክርነት ቃል ወያኔ ለርሃብተኞች ተብሎ ከተቀበለው ርዳታ ውስጥ 95% የሚሆነው ለጦር መሳሪያ ግዢ መዋሉን በእማኝነት መግለጻቸውን ጠቅሷል። በተመሳሳይ መልኩም ይላል የግንቦት ሰባት መግለጫ፤ አቶ ስየ አብርሃ በቅርብ ቀን በጻፉት ጽሁፍ ወያኔ ለርሃብተኞች ይላክ የነበረን የእርዳታ ገንዘብና እህል በርግጥም ለጦር መሳሪያ ግዢ ያውል እንደነበር አረጋግጠዋል።

የግንቦት ሰባት መግለጫ በ1977 ዓም ወያኔ ለርዳታ ይላክለት የነበረውን ገንዘብ ለጦር መሳሪያ ግዢ እያዋለ ባለበት ወቅት ወያኔ መሰረቱን ከጣለበት የትግራይ ክልል ብቻ በሽህ የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች እንደቅጠል ይረግፉ እንደነበር ገልጾ አሁንም ከሃያ አምስት ዓመታት በኋላ የወያኔው አገዛዝ ባለስልጣናት በተመሳሳይ መልኩ ለርዳታ የሚላክን ገንዘብ ለፖለቲካዊ ጥቅም እያዋሉት እንደሆነ አስታውሷል። በመቀጠልም ምንም እንኳን አሁንም ኢትዮጵያ ባሳለፍናቸው ሁለት አስርተ ዓመታት በአፍሪካ የምግብ ርዳታ ተቀባይነት የቀዳሚነቱን ቦታ የያዘች መሆኑ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ግዜ

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አንድ የእንግሊዝ ከፍተኛ ባለስልጣንን ከሰሰ

በእንግሊዝ የአፍሪካ ጉዳዮች ሀላፊ የሆኑት ባሮንስ ጊሊንስ ኪኖክ፣ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በእስር ላይ የሚገኙትን ወ/ት ብርቱካንን እንዲፈታ፣ የውጭ እርዳታ ለፖለቲካ ድጋፍ ማስገኛ ውሏል የሚባለውም ጉዳይ እንዲጣራ መጠየቃቸውን ተከትሎ፣ የመለስ አገዛዝ ባወጣው መግለጫ "የእንግሊዟ ባለስልጣን ጥያቄ ቅኝ የመግዛት ፍላጎቷ አሁንም ድረስ አብሮአት እንዳለ የሚያሳይ ነው" ሲል መልስ መስጠቱን ብሉምበርግ ዘግቧል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ባወጣው መግለጫ፣ "ኪኖክ ተወላጅ ዜጎችን እንደልቧ ለማሽከርከር የምትፈልግ የሚሽነሪ ትምህርት ቤት ሃላፊ ትመስላለች" ሲል የዘለፋት ሲሆን፣ ባለስልጣኑዋ የኤርትራ ደጋፊ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በግንቦት 97 ምርጫ ወቅት መንግስትን ለመገልበጥ አቅደው ሲንቀሳቀሱ ከነበሩ የአውሮፓ ህብረት ልኡካን ጋር የተባበሩ ናቸው ሲል ከሷቸዋል።

ብሉም በርግ በኢትዮጵያ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከመጪው ብሄራዊ ምርጫ ጋር በተያያዘ ተከታታይና ተደጋጋሚ ማዋከብ እየተፈጸመባቸው መሆኑን ና የካቲት 23 ቀን 2002 ዓም አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ከዚሁ ጋር በተያያዘ ህይወታቸው ያለፈ መሆኑን አውስቷል። የኒህን የፓርቲ አባልና እጩ ተወዳዳሪ አሟሟት አስመልክቶ በግድያው የመንግስት እጂ ያለበት መሆኑን መግለጻቸውን ነገር ግን አገዛዙ በበኩሉ መሰረተ ቢስ ውንጀላ ነው በማለት የተለመደ የማጣጣል ማስተባበያ መስጠቱን ድህር ገጹ በዘገባው አመልክቷል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አሜሪካዊው ሴናተር የአሜሪካ መንግስት በኢትዮጵያ እና በአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት አሳሰቡ

ሴናተሩ ማርች 2 ቀን 2010 ዓም ባወጡት ጠንካራ መግለጫ የአባማ አስተዳደር በኢትዮጵያ እና በመጪዎቹ ተከታታይ ወራት ምርጫ ለማድረግ በሚያስቡ የአፍሪካ አገሮች ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ አሳስበዋል። ኢትዮጵያን በአንደኛ ደረጃ በማስቀመጥ ትችታቸውን የሰነዘሩት ሴናተር ፊንጎልድ፣ የአሜሪካ የብሄራዊ ደህንነት ሃለፊ ስለኢትዮጵያ የሰጡትን ምስክርነትበመጥቀስ "መለስ ዜናዊና ፓርቲው በግንቦት97ቱ ምርጫ አይነት የታየው መለስተኛ የፖለቲካ ክፍተት እንዳይደገም አጥብቆ እየተከላከለ ነው" ሲሉ ወቅሰዋል። ሲናተሩ አያይዘውም "በእርግጥም በኢትዮጵያ የሚታየው የዲሞክራሲ መድረክ ከ ግንቦት97 ምርጫ ወዲህ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠበበ ነው። ባለፉት ሁለት አመታት የኢትዮጵያ ፓርላማ የመንግስት ተቃዋሚዎችን እንደልብ እንዲያስርና እንዲያሰቃኝ ነጻ ፈቃድ ሰጥቷል። ከእነዚህ ህጎች መካከል የሲቪል ማህበራትን በመንግስት ቁጥጥር ስር የሚያስገባውና ከአስር በመቶ በላይ ከውጭ አገር ድርጅቶች ድጋፍ የሚያገኙ በሰብአዊ መብቶች፣ በጾታ እኩልነት፣ በህጻናት መብቶች፣ በአካል ጉዳተኞችና በግጭት አስወጋጅ ድርጅቶች ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚያግደው ህግ ይገኝበታል። ሌላው ደግሞ የጸረ ሽብረተኝነት ህግ የተባለው ሲሆን ይህ ህግ ሽብርን በመከላከል ስም ሀሳባቸውን በሰላም ለማራመድ ወይም ለመቃወም የመረጡትን ወገኖች ለማሰር ተብሎ የተዘጋጀ ነው።" ሲል ጽፈዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ የአሜሪካንና የግንቦት7ን ድምጾች እያፈነ መሆኑ ታወቀ

ሲፒጀ በሚል ምህጻረ ቃል የሚታወቀው ዓለም ዓቀፍ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ድርጅት የካቲት 25 ቀን 2002 ዓም ባወጣው ጽሁፍ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአማርኛ ፕሮግራምና የግንቦት7 ንብረት የሆነውን የግንቦት7 ሬዲዮ ፕሮግራሞችንና ዝግጂቶችን ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይደርሱ መደረጉን ገልጿል። ከሲፒጄ መግለጫ በፊት ያሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ወደ ኢትዮጵያ እያሰራጫቸው ያሉት ፕሮግራሞቹ ኤሌክትሮኒክ በሆነ የጠለፋ ዘዴ እየታፈኑና ወደ አድማጮቹ ጆሮም እንዳይደርስ መደረጉን ገልጸ ነበር። ቪኦኤ በዚሁ ሪፖርቱ ዓለም አቀፍ የሆነ የአጭር ሞገድ ስርጪት ክትትል ክፍልንና ከኢትዮጵያዊያን አድማጮቺም የቀረበለትን አቤቱታ በመጥቀስ እንዳረጋገጠው ካለፉት አስር ቀናቶች በላይ ጀምሮ ባለው ጊዜ ከአሜሪካን ሃገር በቀጥታ የሃገሪቱ ዋነኛ ቋንቋ በሆነው አማርኛ የሚተላለፈው ዝግጂት በርግጥም አፈና እየተደረገበት እንደሚገኝ ማረጋገጡን ጠቅሷል። በዚሁ ሪፖርት ላይ በሬዲዮ ስርጪቱ አፈና እየተደረገ መሆኑ ይረጋገጥ እንጂ አፈና ያደረገው አካል እስካሁን በትክክል ያልተለየ መሆኑን ነገር ግን አፈናው እየተፈጸመ ያለው እዚያው ኢትዮጵያ ውስጥ እየተለቀቀ ካለ የኤሌክትሮኒክ ሞገድ መሆኑን መረጋገጡን ገልጿል።

ሲፒጄ ከዚሁ የማጣራት ስራው ጋር በተያያዘ ባቀረበው የጥናት ውጤት ሪፖርቱ እንደ ቪኦኤ የአማርኛ ክፍል ሁሉ የጀርመኑ ዶቺቬሌ የአማርኛ ዝግጂት ስርጪቶች እንዲሁም የግንቦት ሰባት እንቅስቃሴ ራድዮ ፕሮግራሞች ኢትዮጵያዊያን እንዳያዳምጧቸው ተከታታይ የሆነ አፈና የተካሄደባቸው መሆኑን እንዳረጋገጠ በዘገባው ላይ ጨምሮ ገልጿል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አሸዋን በምግብነት ሸጦ በማጭበርበር የመጣን ወያኔን ማስወገድ የሁላችንም ግዴታ ነው!!!

ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት ወያኔ ጆንያዎችን በአሸዋ ሞልቶ - ከላይ እህል በተን አድርጎባቸው - "በችጋር እየረገፈ ላለው ሕዝብ የማደርሰው ምግብ ነው፤ መሸመቻውንና ማጓጓዣውን ቻሉኝ" ብሎ በማጭበርበር በመቶ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የተገመተ ገንዘብ ከግብረሰናይ ድርጅቶች መቀበሉ እና ከዚህ ገንዘብ ውስጥም ዘጠና አምስት በመቶው ለመሣሪያ ግዢና ለማርክሲስት ሌሊኒኒስት ሊግ ትግራይ (ማሌሊት) ማጠናከሪያ መዋሉ ሰሞኑን የብሪታኒያ የዜና አገልግሎት (ቢቢሲ) አጋልጧል።

ዜናው ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን እጅግም አዲስ አይደለም። ግንቦት 7 ይህን የወያኔ ወንጀል በወራት በፊት በርዕሰ አንቀጹም በትንተናዎችም አጋልጧል። ዜናው አዲስም፣ አስደንጋጭም የሆነባቸው የወያኔ ወዳጅ የሆኑ መንግሥታትና የእርዳታ ድርጅቶች ናቸው። አንዳንዶቹ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር የሰው ልጅ ሊፈጽም ይችላል ብለው አምነው ለመቀበል ተቸግረዋል። ከፊሎች በተፈፀመው ክህደት በእጅጉ አዝነዋል፤ ተናደዋል። ጥቂቶች በበጎ አድራጎት ሥራ ውጤታማነት ላይ ተስፋ አጥተዋል። አንዳንዶች ደግሞ ጉዳዩ እነሱንም ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸው ስለሚያውቁ ባለ በሌለ ኃይል መከላከልን መርጠዋል።

እኛ ኢትዮጵያዊያን ግን ከዚህም የባሰ እያየን ነው። የእርዳታን ገንዘብ አጭበርብሮ በገዛው መሣሪያ እና በወቅቱ ዓለምዓቀፋዊና አገራዊ ሁኔታዎች ተረድቶ ሥልጣን ላይ የወጣው ወሮበላ ዛሬ ለም መሬታችንን እየመረጠ ለቻይና፣ ህንድና አረብ ቱጃሮች መሸጡ፤ ዳር አገር ገምሶ ለሱዳን መሸለሙ፤ በጉዲፈቻ ሽፋን ህፃናትን እየሸጠ መሆኑ፤ በሥራ ሽፋን እህቶቻችንን ለግርድናና ሌላም እኩይ ተግባራት ወደ አረብ አገራት መላኩን ማጧጧፉ፤ እርስበርሳችን ማናከሱ፤ በሰበብ አስባቡ የጅምላ ፍጅቶችን መፈፀሙ አሸዋን በእህልነት ከመሸጥ የከፉ ተግባራት ናቸው። በሌብነት ያደገ ድርጅት በሌብነት መሰልጠኑ የሚጠበቅ ነው።

በሬ ሰርቆ የተያዘ ልጇን "ተዋርደህ፣ አዋረድከኝ" ባለችው ጊዜ "ምነው እማ ድሮ በእንቁላሉ ጊዜ እንዲህ አላልሺኝ?" አላት ይባላል።

ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት ወያኔ በእርዳታ እህል ላይ ስላደረገው ማጭበርበር ዛሬ ቢቢሲ ማውራቱ እና የወያኔን እኩይነት ለዓለም ማጋለጡ መልካም ነገር ነው። ሆኖም ዓለም ገና ያልተገነዘበው ሃቅ ያኔ የተደረገው የእንቁላል ስርቆት መሆኑ ነው። ዛሬ ዝርፊያው በሬ ላይ ደርሷል። የያኔው ዝርፊያ ብዙ ቢሆንም በሚሊዮኖች መገመት ተችሏል። ዛሬ እየዘረፈ ያለውን ሃብት ብዛት ለመገመት ግን ቢሊዮኖችም አይበቁም። ህፃናትንና እህቶቻችንን በዋጋ መተመን አይቻለንም። ከመሬታችንም ጋር ነፃነታችንንም እያጣን ነውና የመሬታችንንም ዋጋ ማስላት ከንቱ ልፋት ነው። ያጣነውን ውስጣዊ ሰላምና መከባበርም በዋጋ መገመት ያዳግታል። ወያኔ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን በጅምላም በችርቻሮም እየሸጠ ነው።

ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት ከትግራይ የችጋር ሰለባዎች ጉሮሮ ነጥቆ ንግድ የጀመረው ማኅበረ ረድኤት ትግራይ /ማረት/ ዛሬ የመላዋን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን ደም በመምጠጥ ጎልብቶ ኤፈርት ሆኗል። ከእርዳታ በተዘረፈ ገንዘብ በከተሞች ውስጥ የተገነቡና አሁንም በመገንባት ላይ ያሉ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ወያኔ አመጣሁ የሚለውን "ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት" ማሳያዎች ሆነዋል። ችጋር "ጨስ አልባ" ትርፋማ እንዱስትሪ በመሆን ወያኔን ከትቢያ አንስቶ አሁን አለበት ደረጃ አድርሶታል። ወያኔ ነጋ ጠባ ስለ ድህነት ቅነሳ መደስኮሩ እና ለዚህም ጆሮ የሚሰጡ መኖራቸው የሚነግረን ነገር ቢኖር ችጋር ወያኔን በስልጣን የመቆያ ምክንያት በመሆንም ጭምር ውለታ እየፈፀመለት መሆኑን ነው። ችጋር ባይኖር ኖሮ ወያኔም ባልኖረም ነበር። ችጋርና ወያኔ እርስ በርስ እየተመጋገቡ የፋፉ ጥብቅ ወዳጆች ናቸው።

ወያኔ ከችጋር ጋር የጠበቀ ወዳጅነትን የፈጠረው ቆምኩለት በሚለው የትግራይ ሕዝብ ቸነፈር መሆኑ የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም። ሌብነት ከቤት መጀመሩ የተለመደ ነው። ቤተሰብም ሌባን - ልጅ ነውና - እየተከላከለ ያሳድጋል። የወያኔና የትግራይ ዝምድና የሌባው ልጅና የሌባ እናትን ይመስላል። ትግራይ በምሳሌው ውስጥ ካለችው እናት በባሰ አምርራ ወያኔን "ተዋርደህ፣ አዋረድከኝ፤ ወግድልኝ" ልትለው ይገባል። ወያኔ በረሃ ሆኖ ላላዘነለት ሕዝብ ቤተመንግሥት ውስጥ ሆኖ ያዝንለታል ማለት ዘበት ነው። አሸዋን በእህልነት የሸጠ ቡድን መንግሥት ነኝ ብሎ ለሃያ አመታት መቆየት መቻሉ የሁላችንም እፍረት ነው።

በቢቢሲ የሰሞኑ ዘገባ መነሻነት የሚከተሉትን መልዕክቶች ማስተላለፍ እንፈልጋለን።

1. ለጋሽ አገራት ለኢትዮጵያ በሚሰጡት እርዳታ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲያደረጉ ኢትዮጵያውያን ሲማፀኑ የቆዩት የእርዳታ ምግብ፣ ቁሳቀስና ገንዘብ ለታሰቡላቸው ዓላማዎች እንደማይውሉ ከጥርጣሬ ባለፈ በተጨባጭ ስለሚያውቁ ነው። የወያኔ እርዳታን ለፓለቲካ እና ለግለ ጥቅሙ የማዋል እኩይ ተግባር ሃያ አመታት ያሳለፈ፣ ጊዜው ያለፈበት ታሪክ ሳይሆን ዛሬም በየእለቱ እየተደረገ ያለ ጉዳይ ነው። ለጋሽ አገራት ለችግራችን ለመድረስ በመፍቀዳቸው እናመሰግናለን፤ ሆኖም ግን የሚሰጡት እርዳታ ለድሃው መዳኛ እንጂ መጥፊያ እንደማይሆን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለባቸው ደግመን ደጋግመን እናሳስባለን።
2. የወያኔ ሹማምንት ከእርዳታ ከዘረፉት ገንዘብ ውስጥ በርከት ያለው መጠን እዚያው እርዳታውን በሰጡት አገራት ባንኮች ውስጥ በራሳቸው በሹማምንቱ፣ በቤተሰቦቻቸውና በታማኝ ባለሚሎቻቸው ስም የሚገኝ በመሆኑ በገዛ ራሳቸውም አገር ውስጥ አጠቃላይ ምርመራ እንዲያደርጉ እንጠይቃለን።
3. ለጋሽ አገራትና ግብረሰናይ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለስማቸው ሲሉ የአምባገነኖችን አሳፋሪ ሙስና ከመሸፋፈን እንዲታቀቡ፤ ይልቁን በድህነት ሰበብ እየከበሩ ያሉት የወያኔ እኩያንን እንዲያጋልጡ አጥብቀን እናስገነዝባለን።
4. መረጃዎችን ለቢቢሲ ዘጋቢ የሰጡ ዜጎቻችንን ቁርጠኝነት እያደነቅን ሌሎችም የእነሱን አርዓያ ተከትለው የሚያውቋቸውን መረጃዎቻችን በሙሉ ይፋ በማድረግ ወያኔን እርቃኑን እንድናስቀር ጥሪ እናደርጋለን።
5. በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ወያኔን የማጋለጥ ተግባር አጠናክረው እንዲቀጥሉ እናበረታታለን።

በመጨረሻም ሁላችንንም ለዚህ ሃገራዊ እፍረት የዳረገንን ወያኔን አስወግደን በምትኩ ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመገንባት ቆርጠን እንነሳ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## ጀኖሳይድ ወች የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት . . . ከገጽ 1 የዞረ

በሴፕቴምበር 24 ቀን 2003 ዓም በ መለስ ዜናዊ ቤሮ ውስጥ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አዲሱ ለገሰ፣ የህወሀት ባለስልጣን የሆነው ስብሀት ነጋ፣ የማስታወቂያ ሚኒስትር በረከት ስምኦን፣ የጋምቤላ የደህንነት ሃለፊ አሞት አባንግ አሎም፣ የፌደራል ደህንነት ሃለፊ አለማየሁ፣ የፌደራል ጉዳዮች ሀላፊ አባይ ጸሀዬ፣ ኢታማጆር ሹም ሳሞራ ( ሙሀመድ) የኑስ፣ የመከላከያ ሰራዊት የስለላ ሃለፊ ብርጋዴር ጄኔራል ዮሀንስ ገብረመስቀል፣ እንዲሁም የመከላከያ ሚኒስትር አባዱላ ገመዳ በጋምቤላ ያለውን የጸጥታ ሁኔታ ለመወያየት ተሰብስበው የዲሰምበር 13 ፣ ቀን 2003 ዓም ጭፍጨፋ እንዲጀመር ውሳኔ አስተላልፈዋል ሲል የጀኖሳይድ ወች ድብዳቤ ጠቅሷል።

በጀኖሳይድ ወች ምርመራ መሰረት ግድያው የተፈጸመው በጊዜው በጋምቤላ ተመድቦ በነበረው የመከላከያ ሰራዊት አዛዥ ጴጋየ በየነ ትእዛዝ ሲሆን፣ ትእዛዙን በቀጥታ ያገኘውም በወቅቱ የፌደራል ጉዳዮች ከፍተኛ ባለስልጣን ከነበረው ዶ/ር ገብረአብ በርናባስ ነበር። ታደሰ ሀይሌ የተባለው የፖሊስ አዘዥም ትእዛዝ በመስጠት መሳተፋትን ድርጅቱ ገልጿል።

የጭፍጨፋው ዋና ምክንያት አካባቢውን በነዳጅ ፍለጋ ላይ ለተሰማሩት የቻይና ኩባንያዎች ለማስረከብ ሲሆን፣ አሁን እየታየ ባለው ሁኔታ አኝዋኮችን ከቦታቸው ለማፈናቀል ሌሎች ከፍ ያሉ ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ድርጅቱ አስታውሷል።

ባለፉት ወራት አኝዋኮች የሰፈሩባቸው ቦታዎች ለቻይናውያን፣ ለህንዶችና ለጃፓኖች ለ99 አመታት ለሚቆይ የጊዜ ገደብ እጅግ አነስተኛ በሆነ ክፍያ መሰጠታቸውን የገለጸው ድርጅቱ፣ እነዚህ ስምምነቶች ሲደረጉ አኝዋኮች እንዲሳተፉ አለመደረጋቸው ብቻ ሳይሆን፣ እርምጃው መለስ ዜናዊን በአለም ላይ ካሉ ቱጃር አምባገነኖች መካከል አንዱ እንዲሆን አድርጎታል ብሎአል።

ሰዎችን ያለፍላጎታቸው በዘራቸው፣ በፖለቲካ እምነታቸው፣ በባህላቸው፣ ወይም በሀይማኖታቸው ከቦታቸው እንዲነሱ ማድረግ በአለማቀፍ የወንጀል ህግ ወይም የሮማ ድንጋጌ እየተባለ በሚጠራው ህግ አንቀጽ ሰባት መሰረት (ከላይ ይቀጥላል) ወንጀል መሆኑን ድርጅቱ ጠቅሶ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች አስከባሪ ኮሚሽን የራሱን ህዝቦች እያሸበረ የሚገኘውን የኢትዮጵያ መንግስት ከድርጊቱ እንዲታቀብ ለማድረግ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል ሲል ጥሪውን አሰምቷል።

ድርጅቱ በጊዜው በጭፍጨፋው ተሳትፈዋል ያላቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ያወጣ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ረዳት ኢንስፔክተር ታደሰ መሬሳ፣ ረዳት ኢንስፔክተር አክሊሉ ሰካታ፣ ረዳት ኢንስፔክተር ተሸሞ ካባ፣ ሰርጂንት ንጋቱ እንግዳ፣ ሰርጂንት አበበ ጣሰው፣ ሰርጂንት አትጉ ግርማይ ፣ ሰርጂንት ገረሙ ወርጂ፣ ኢንስፔክተር ሙሀመድ ካሳ. የቡድን መሪ ደምሴ ባልቻ፣ ፖሊስ ሽብሩ ረጋሳ፣ ፖሊስ ሙለታ ቶሎሳ፣ ፖሊስ ጌታቸው ደምሴ፣ ፖሊስ አበራ በቀለ፣ ፖሊስ አሸናፊ ታደሰ፣ የቡድን መሪ በፈቃዱ አሰፋ፣ ፖሊስ ከድር አሊ፣ ፖሊስ ከበደ እንዳለ፣ የፖሊስ አዛዥ ታደሰ ሀይለስላሴ፣ ፖሊስ ከበደ ተኪሳ፣ ፖሊስ ታደለ አየለ፣ ግርማ ሊጂ፣ ግርማ ተረፈ፣ ዱባለ ተሰማ፣ አድኖ ለገሰ፣ ገበያው አድሳ፣ አየለ ታደሰ፣ ወንድሙ ፈይሳ፣ እንዳለ ጃለታ፣ ክኔሳ ጨዋካ፣ መስካለ ዲቻ፣ ሽብሩ ሬታ፣ ኩንዳ የተባለ የፖሊስ ጤና ክፍል ሃላፊ እና መኮንን የተባለ የፖሊስ የደህንነት ሀላፊ ይገኙበታል።

## የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አንድ የእንግሊዝ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በሌላ ዜና ደግሞ በአራት የጋዜጣ አሳታሚዎች ላይ የወያኔው ፍርድ ቤት በትናንትናው እለት ውሳኔ መስጠቱን የሀው ድህር ገጽ ጠቅሷል። ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ ክስ ተመስርቶባቸው በእስር ከቆዩ በሁዋላ በነጻ የተለቀቁት የአራት ጋዜጣ አሳታሚዎች፣ በድርጅቶቻቸው ላይ የተጣለውን ቅጣት እንዲከፍሉ የጠቅላይ ፍርድቤት ውሳኔ አስተላልፎአል። ጠቅላይ ፍርድቤቱ የስር ፍርድቤት የሰጠውን ውሳኔ በመገልበጥ አሳታሚዎቹ የገንዘብ ቅጣቱን እንዲከፍሉ የወሰነ ሲሆን፣ ይህ እርምጃ ሌሎች ጋዜጠኞች መጪውን ምርጫ በተመለከተ አገዛዙን የሚተች ምንም አይነት ጽሁፍ እንዳያቀርቡ ለማስፈራራት ተብሎ የተወሰደ መሆኑን አሳታሚ ሲሳይ አጌና፣ ሰርካለም ፋሲልና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ባወጡት መገልጫ ጠቅሰዋል። በውሳኔው መሰረት ሰርካለም አሳታሚ 120 ሺ ብር፣ ኢትዮጵ አሳታሚ 100 ሺብር፣ ዘካርያስ አሳታሚ 60 ሺብርና ፋሲል አሳታሚ 15 ሺ ብር ገቢ እንዲያደርጉ ታዘዋል።

## ውጭ ጉዳይ ሲገለጥ
## *የስዩም ነገር*

**ክፍል 1**

ውጭ ጉዳይ ሚ/ር ከብሔራዊው ቤተ-መንግሥት ዝቅ ብሎ ከሂልተን ሆቴል ፊት ለፊት ይገኛል። ይህ መስሪያ ቤት ከነ ሙሉ ክብሩና ጥቅሙ ለስዩም መስፉን ከተሸለመ እነሆ 18 ዓመት ሆነው። የዚህ ሰው ቢሮም በህንጻው በሰተሰሜን ጥግ አራተኛው ፎቅ ላይ በቀይ ምንጣፍ ተሸልሞ ይታያል። በሦስትኛዉ ፎቅ ላይ ከስዩም መስፍን ቢሮ በስተ-ደቡብ አንዲት ፐብ (pub) የምትምስል ክፍል በቀይ ምንጣፍ አሸብርቃና በባለ ቀልሞቹ መጠጦች ቶሞልታ ሁሌም ዝግጁ ሁና ትገኛለች።በዚህች ክፍል ስዩም መስፍን ከሂለተን ሆቴል ምግብ እያስመጣ ለወዳጆቹ ግብር ያበላበታል ከስራ ሰዓት ውጭም የመስሪያ ቤቱን ታማኝ ሎሌዎች ስብሰባ ይጠራና ብሉ ጠጡ ደስም ይበላችሁ እያለ ሌሎቹን የመስሪያ ቤቱን ሰራተኞች ሁኔታ እየገመገመ ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል።

በዚህች ክፍል ውስጥ በተደረገ ስብሰባ የአንድ ጎበዝ ሰራተኛ ስም ተነሳ።ስዩም መስፍን ከተሽከርካሪ ወንበሩ ላይ ዘና ብሎ ቁጭ እንዳለ የአስተዳደርና ፋይናንስ ሃላፊ ዘርይሁንን ትኩር ብሎ እየተመለከተ“ ለመሆኑ እንዲህ አይነት ሰራተኛ እዚህ መስሪያ ቤት እንዴት ተቀጠረ ?” ብሎ ጠየቀው።ዘርይሁንም “በስህተት” ነው አለ። “በል እንግዲህ ባሰቸኳይ አሰናብተው” ብሎ ቀጭን ትእዛዝ እንደሰጠው በዚያች ቀን በስብሰባው ላይ የተሳተፈ አንድ የትግራይ ወዳጄ ነግሮኛል።ዘርይሁንም ምንም ሳያመነታ ውሳኔውን ለማስፈጸም ተጣደፈ።አንዲት ጥሩ ደብዳቤ ጽፎና ፈርሞ ትግሉ ማናየሁ ማንደፍሮት የተባለ የመ/ቤቱን ሰራተኛ በችሎታ ማነስ ብሎ አባረረ።

ትግሉ ከመቀሌ ዩንቨርስቲ በኢኮኖሚክስ ተመርቆ መ/ቤቱ ባወጣው ማስታወቂያ መሰረት ተወዳድሮ የተሻለ ውጤት በማግኘቱ የተቀጠረ ነበር።ይህ ወጣት ልጅ በእንግሊዘኛ ቋንቋ በሚታተመዉ ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ መንግሥትን የሚተች ጽሁፍ ስለጻፈ ስዩም መስፍን በችሎታ ማነስ ብሎ እንዲባረር ወሰነ።በዚህም የመ/ቤቱ ሰራተኞች ማንኛውንም የመንግስት ድርጊት ከማወደስ በቀር መተቸት እንደማይችሉ አድርጎ የሰራተኛዉን የመናገር ነፃነት ገፈፈዉ።በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል በተነሳው ውዝግብ የድንበር አካላይ ኮሚሽን የሰጠውን ውሳኔ በትክክል አንብቦ መረዳት የማይችል ሚንስቴር ባለበት መ/ቤት አንድ ሰራተኛ በችሎታ ማነስ ተብሎ ሲባረር ታዝበን በጎ ባልሆነ ዝምታ ተዋጥን።ለማንኛውም ያ ጎበዝ ወጣት ልጅ ተባረረ። እነርሱ እየበሉና እየጠጡ ሌላውን በተለይ አማራዉንና ኦሮሞዉን ከስራ ገበታው ላይ አፈናቅለው ጦሙን ያሳድሩታል።እኛ የምናዉቀዉ የወያኔዎች ነፃ ማዉጣት ማለት ይሄዉ ነዉ እንጂ ሌላ የለም።

ይህ መ/ቤት የስዩም መስፍን የሹመት ቦታ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ገንዘብ የሚያጋብስበትም የቢዝነስ ተቋም ነው።በህወሃት ውስጥ የድሃ ገንዘብ መዝርፍ የሚያሳፍርም የሚያስጠይቅም ተግባር ስላልሆነ ስዩም በሚፈጽመው ሙስና የህወሃት አባላት አይገረሙ ይሆናል።።እስከ አሁን እዳየነውና እንደስማነው በህወሃት ባህል መሰረት ማጭበርበር መስረቅ መዋሸት መግደል ጀግንነት ነዉ እንጂ የሚያሳፍር ብልሹ ተግባር አይደለም።ህወሃትን ሌላ በምን እናዉቀዋለን ከዚህ ከረከሰ መግባሩ ዉጭ ? እንዲህ አይነቱን ዝርፊያ አይተንና ሰምተን ከመገረም አልፈን አገሪቷን እንመራለን ብለው የተሰየሙ ሰዎች እንዲህ በተደራጀ ዝርፊያ ውስጥ በመሰማራታቸውና እንዲህ አይነት የሞራል ዝቅጠት ውስጥ በመገኘታቸው ይህም ደግሞ በገዛ አገራችን እየተፈጸመ መሆኑን ስናውቅ አንገታችንን ደፍተን በቁጭት ተቃጠልን።

መቸስ ሰውየው የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ነውና አገሪቷን እየወከለ በየአገራቱ የመመላለስ ልዩ መብት አለው። ከአገር ሲወጣና ሲገባ እርሱ የያዘው ወይም ደግሞ በኮንቴይነር አስጭኖ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባዉ እቃ አይፈተሽም።የፈለገውን ይዞ ይወጣል ያሻውን ደግሞ ይዞ ይገባል።በአንድ ወቅት መርካቶ ውስጥ በአንዲት ሻይ ቤት ውስጥ የሞባይል ስልኮች ከገበያ ዋጋ ባነሰ ይሸጡ ነበር።ለምሳሌ 1000 ብር የሚሸጥ ሞባይል ቀፎ ከዚያ ቦታ ላይ 700 ብር ሲሸጥ እንደነበረ እናዉቃለን።ይህን ንግድ የሚያካሂዱት የውጭ ጉዳይ ሰዎች ሲሆኑ ግብይቱ በሚካሄድበት ወቅት ደግሞ መሳሪያ የታጠቁና የፖሊስ ዩኒፎርም የለበሱ ሰዎች ብርቱ ጥበቃ ያደርጋሉ።ሌላው ነጋዴ የአገሪቷ ህግ በሚፈቅድለት መሰረት ቀረጥ ከፍሎ ግብር አስገብቶ ያዋጣኛል የሚለውን ዋጋ ተምኖ ገዢ ሲጠብቅ ስዩምና ወዳጆቹ ግን አየር ባየር እያጧጧፉ ገንዘባቸውን ያጋብሱታል።ህጋዊ ነጋዴዉን ከገበያ ውጭ እያደረጉ አገሪቷን ወደ መቀመቅ ያወርዷታል።

ስዩም ወደ ውጭ በተጓዘ ቁጥር ከመ/ቤቱ ወጭ እየተደረገና በሶምሶናይት እየተሞላ ይዞ የሚወጣው ገንዘብ አንድም ቀን ተወራርዶ አያውቅም።ይዞ ከሄደው ገንዘብ ምን ያህሉን ተጥቅሞ ምን ያህሉን እንደመለሰ የሚያሳይ የሂሳብ መዝገብ የለም።በአንድ ወቅት ጅቡቲ የደርሶ መለስ ጉዞ ለማድረግ $20000(ሃያ ሽህ) ዶላር ከሂሳብ ክፍል ወጪ ተደርጎ እንደተሰጠው ለሂሳብ ክፍል ቅርበት ስላለኝ አይቻለሁ። ለደርሶ መልስ ጉዞ ይህን ያክል ይዞ ከሄደ ሶስትና አራት ቀን በሚቆይበት ግዜ ምን ያክል ዶላር ይዞ እንደሚወጣ አንባቢ ልብ ይበል።ይህ ሁሉ ብር ጥቃቅን/ልዩ ልዩ ወጭ ተብሎ ይመዘገባል። ከዚህ ብርም ተመልሶ ወደ መ/ቤቱ ካዝና የሚገባ የለም።በዚህ ሁኔታ ስዩም ወደ ውጭ አገር በተጓዘ ቁጥር እየተሸከመ የሚወጣውን ብር አንድም ቀን ኦዲተር አይቶት ስለማያውቅ መጠኑን እንኳን ሌላ ሰው ራሱ ስዩምም ቢሆን አያውቀውም።ይህ ሰው በስልጣን ዘመኑ በዚህ መልክ የዘረፈው ገንዘብ ከእርሱ ትውልድ መንደር አዲግራት አንስቶ እስከ አዲስ አበባ አስፋልት መንገድ ሊያሰራ ይችላል ብል ማጋነን አይሆንብኝም።

ይህ ሰው ምንም የሞራል ለከት የሌለው መሆኑን አቶ አረጋዊ በረጎ “አጉል ሙገሳ ወይስ እውነተኛ ታሪክ?” በሚለው ጽሁፋቸው ላይ ጽናት(ውዳሴ ስዩም) የተባለውን መጽሃፍ ሲገመግሙ ፀሀፊዉ ስለ ስዩም ታሪክ የተናገረውን ስድስት ትላላቅ ታሪካዊ ውሸቶችን አውጥተው አሳይቶናል። እነዚያን የስዩም ውሸቶች እዚህ ላይ ብንጠቅሳቸው ምን ይለናል ? ***ውሸት ቁጥር አንድ ስዩም በ1965 የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ሊቀመንበር ሆኖ ተመረጠ፤ ውሸት ቁጥር ሁለት ስዩም ሙሴን ለማስፈታት የሸረን ኦፕሬሽን መራ ፤ውሸት ቁጥር ሶስት ስዩም የዲማ ማርዋ ማስልጠኛ መሪ ነበር፤ ውሸት ቁጥር አራት ሱዩም የሃይል መሪ ሁኖ ሽራሮ ላይ ወደ ውጊያ ገባ ፤ውሸት ቁጥር አምስት ስዩም የድርቅን ችግር በመፍታት መሪ ነበር፤ውሸት ቁጥር ስድስት ስዩምና በርሁ(አረጋዊ ማለት ነው) በአንድ ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር።*** ።***ይህ*** ሁሉ ውሸት በትግሪኛ ቋንቋ በተጻፈው ጽናት በተባለው መጽሃፍ ውስጥ ይገኛል። ጸሃፊውም ሀይላይ የሚባል ወጣት ነው።ለዚህ ጸሃፊ የመረጃ ምንጩ ደግሞ ስዩም መስፍን ነው ብሎ አቶ አረጋዊ በርሀ አረጋግጠው ነግረውናል።ሃይላይ ስዩምን እየጠየቀ ስለ ስዩም ገድል ጽፎ ሲያበቃ ለስዩም አሳየው ስዩምም ደስ ብሎት እንዲታተም መልካም ፈቃዱ ሆነ።ይህ ማፈሪያ የሆነ ከንቱ “ውዳሴ ስዩም” ከነ ውሸቱ በገበያ ላይ ይኖራል።እንግዲህ ስዩምን ድርቅ ባለ ውሸቱ ካልሆነ በቀር ሌላ በምን እናውቀዋለን? ስዩም ምንም ሳያፍር በድፍረትና በኩራት የኛ ያልሆነውን መሬት ከጠበቅነው በላይ ተሰጥቶናል ብሎ በተሌቭዥን መስኮት ሲናገር አይተነው አንገታችንን ደፍተን አዝነን አላበቃንምን?

### *የድንኳኑ ነገር*

አንድ አንቶኖቭ ከአምስተርዳም ፊሊፕስ ካምፓኒ እቃ ጭኖ ወደ አዲስ አበባ ይገሰግሳል።ዘውትር እንደሚደረገው አንድ አውሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ከውጭ ጉዳይ የመግቢያ ፈቃድ ማግኘት ይጠበቅበታል።ይህ ፈቃድ የሚሰጠው በፕሮቶኮል ዋና ዳይሬክቶሬት ስር ባለ አንድ ዋና ክፍል አማካኝነት ነው።የሚመጣው አንቶኖቭ ንብረትነቱ የሩሲያ በመሆኑ በኢትዮጵያ የሩሲያ ኢምባሲ ጉዳዩን ይከታተለዋል። በዚሁ መሰረት የመግቢያ ፈቃድ ለማግኘት አንድ የሩሲያ ኤምባሲ ዲፕሎማት አንቶኖቩ የጫነውን የኢቃ ዝርዝር ይዞ ከፈቃድ ሰጪው ሰው ቢሮ ከተፍ ያላል።ይህን እዚህ ጋ እንተወውና ከዚህ በፊት ወደ ሆነው ክስተት እንሂድ።

አንድ ስልክ ከትግራይ ክልል ከወ/ሮ አረጋሽ (የወቅቱ የክልሉ መስተዳድር ዋና ጸሃፊ የነበሩ ናቸው) ቢሮ ወደ ፈቃድ ሰጪው ሰው በሮ ይደወላል።ፈቃድ ሰጪው ሰው እንዲህ ካሉ ከፍተኛ ባለስልጣን ስልክ ተደውሎለት ስለማያውቅ ግራ ይገባውና በታላቅ ትህትና “እመቤቴ ተሳስተው እንደሆን እኔ የበታች ሰራተኛ ስለሆኑኩ እርስዎን ሽቅብ ወደ ላይ ለማናገር አልችልም ወደ ሚ/ሩ ቢሮ ላስተላልፎትና እሳቸውን ቢያናግሩ ይሻላል ይላቸዋል” ሴትየዋም “አዎን ልክ ነህ ወደ ላይ እኔን ለማናገር አትችል ይሆናል ግን እኛ ከፈለግን የማናገር ግዴታ አለብህ” ይባላል። አሁንም በትህትና “እሺ እመቤቴ ምን ልታዘዝ ታዲያ?” “አሁን ከአምሰተርዳም ***ለሰደተኞች የሚሆን ድንኳን ተጭኖ እየመጣ ስለሆነ አንቶኖቩ ቀጥታ መቀሌ እንዲያርፍ እንዲደርግ ብለው ቀጭን ትእዛዝ ይሰጡታል***”።ይህ በፈቃድ ሰጪው የስራ ዘመን ሁኖ የማያውቅ እንግዳ ነገር ነበር።ፈቃድ ሰጪውም በትህትና “እመቤቴ ይህ ነገር ከእኔ የስራ ሃላፊነት ውጭ ስለሆነ እንዲህ ማድረግ አልችልም ምናልባት ክቡር ሚ/ሩን ቢያነጋግሩ” ይላቸዋል። “ስዩምን ስላጣሁት ነው” ይሉታል።”እንግዲያውስ ዋና ዳይሬክተሩን ቢያናግሯቸው” ሲል “እሱም ቢሮው የለም ስለተባልኩ ነው”። “እመቤቴ ያሉኝን እኔ ማድረግ አልችልም ልዩ ፈቓድ የሚያስፈልገው ስለሆነ ለአለቆቼ ቢነግሯቸው ይሻላል እኔ መፍቀድ የምችለው አዲስ አበባ እንዲያርፍ ብቻ ነው”። “መልካም በል ተወው” ይባልና ስልኩ ጆሮው ላይ ይዘጋል።ከዚህ በኋላ አቶ ንዋይ ገ/አብ(የጠቅላይ ሚ/ሩ የኢኮኖሚ ጉዳዮች አማካሪ ናቸው) ወደ ፈቃድ ሰጪው ቢሮ ይደውላሉ።አሁንም ፈቃድ ሰጪው ግራ ይገባዋል ለማንኛውም ብሎ ምን እንደሚፈልጉ ይጠይቃቸዋል።”ከአምስተርዳም የሚመጣው አንቶኖቭ መቀሌ እንዲያርፍ እንፈልጋለንና ፈቃዱን እንድተፈርምና ለሚመለከተው ክፍል እንድታሳውቅ ይሉታል”።ፈቃድ ሰጪውም “ጌታየ እኔ ይህን ማድረግ እልችልም ከሃላፊነቴ ውጭ ስለሆነ ለአለቆቼ ቢነግሯቸው እነሱ ሊፈቅዱ ይችላሉ” ይላቸዋል። “አለቆችህ የሉም ስለተባልን ነው እኮ አንተን የምናናግረው”። “ቢሆንም እኔ ይህን ማድረግ አልቸልም”። በል ተወው ይባልና ስልኩ ጆሮው ላይ ይጠረቀማል።

በዚህ ጊዜ የሩሲያው ዲፕሎማት አንቶኖቩ የጫነውን የእቃ ዝርዝር ይዞ ወደ ፈቃድ ሰጪው ቢሮ መጣ። ዲፕሎማቱ ይዞ በመጣው የእቃ ዝርዝር መሰረት አንቶኖቩ የጫነው ቱባ ቱባ ባለስልጣናቱ እንደሚሉት ***ለስደተኞች የሚከፋፈል ድንኳን ሳይሆን ከፊሊፕስ ካምፓኒ የተጫኑ ልዩ ልዩ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ነበር***።ፈቃድ ሰጪውም እጅግ ተገረመ ውስጡን አንዳች አይነት ክፉ ስሜት ሲበላው ተሰማው።የሆኖ ሆኖ የመግቢያውን ፈቃድ የሩሲያው ዲፕሎማት ባቀረበለት ሰነድ መሰረት ፈርሞ ወዲያውኑ ለሚመለከተው ክፍል(ለደህንነት፤ለመከላከያ እና ለሲቪል አቪየሽን መ/ቤቶች) አስተላለፈ።በፈቃድ ሰጪው ግምት አዲስ አበባ ካረፈ ነገሩ በሚመለከተው ክፍል እርምጃ ይወሰድባታል ብሎ አስቦ ነበር በፍጥነት ፋክስ ያደረገላቸው።ሆኖም ግን ነገሩ እንዳሰበው አልሆነም።የሩሲያውም ዲፕሎማት አንቶኖቩ ወደ ኢትዮጵያ አየር ክልል መግባት እንደሚችልና አዲስ አበባ እንደሚያርፍ ተነግሮት አመስግኖ ወደ መጣበት ተመለሰ።

ከዚህ በኋላ የሆነው ግን ለፈቃድ ሰጪው ሰውየ አስፈሪ ነበር።በድጋሚ ሁለቱ ትላልቅ ባለስልጣናት ይደውላሉና ይህን መራጃ ከየት እንዳገኘና ለምን አዲስ አበባ እንዲያርፍ ፈቃድ እንደሰጠ ያፋጥጡታል።ፈቃድ ሰጪውም የዋዛ አልነበረምና አንደኛ ይህ ጉዳይ በቀጥታ እኔን የሚመልከት ነው ሁለተኛ እናንተ ያላችሁት ድንኳን ገና አልመጣም ይህኛው አውሮፕላን የጫነው ድንኳን ሳይሆን ኤሌክትሮኒክስ ነው ይላቸዋል። ሁለቱም ባለስልጣናት ከዚህ በኋላ የሚሉት ነገር ስለሌላቸው ስልኩን ጆሮው ላይ እየዘጉ ወደ ሚቀጥለው ተግባራቸው ተሰማሩ።አንቶኖቩን መቀሌ ማሳረፍ።በዚህም በዚያም ተብሎ አንቶኖቩ ከነ ሙሉ እቃው ሌላ ፈቃድ ከውጭ ጉዳይ ሳያስፈልገው መቀሌ እንዲያርፍ ተደረገና እቃውም እዚያው መቀሌ ላሉ ሽሪኮች እንዲከፋፈል ተደረገ። ይህ እንግዴህ የመንግስት ታክስ/ቀረጥ ያልተከፈለበት መሆኑን ልብ በሉልኝ።

ክፍል 2 በሚቀጥለው ሳምንት ይቀርባል

## ጀኖሳይድ ወች የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት ለፍርድ እንዲቀርቡ በድጋሜ አሳሰበ

የድርጅቱ ፕሬዚዳንት የሆኑት ዶ/ር ግሪገሪ ስታንተን ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ለሆኑት ለዳኛ ናቫንቴም ፒለይ በጻፉት ደብዳቤ “ከዲሰምበር 13 እስከ ዲሰምበር 16 ፣2003 ዓም በተደረገው ጭፍጨፋ ለተገደሉት 424 አኙዋኮች ተጠያቂ የሆኑ ሰዎች እስከዛሬ ድረስ ለፍርድ አለመቅረባቸውን ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንቱ በደብዳቤያቸው “በ2004 ዓም በተመሳሳይ መልኩ ለተገደሉት ከ1ሺ በላይ አኙዋኮችም ተጠያቂ የሆኑ ሰዎች እስከዛሬ ለፍርድ አልቀረቡም። በ2004 ዓም ጀኖሳይድ ወች ባደረገው ማጣራት የኢትዮጵያ መንግስት አቅዶ በርካታ አኝዋኮችን መግደሉንና ግድያውን ለመሸፋፈን ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን ጠቅሷል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግሰት በኢትዮጵያና በሶማሊያ በርካታ ተመሰሳሳይ ወንጀሎችን ፈጽሞአል። በኦጋዴንም እንዲሁ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሞአል። ይህን የፈጸሙ ሰዎችን በዝምታ የማለፍ ባህል እየተስፋፋ ነው” ሲሉ ገልጸዋል።

አሁን የቀረበው ደብዳቤ ጀኖሳይድ ወች በማርች 2009 ዓም ለ ተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኮሚሽነር ለጻፈው ድብዳቤ ቀጣይ ክፍል ሲሆን፣ በመጀመሪያው ደብዳቤ ድርጂቱ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጸመ ያለውን ወንጀል የተባበሩት መንግስታት ድርጂት እንዲያጣራ ጠይቆ እንደነበር ይታወሳል። እስከዛሬ ድረስ ግን ለጥያቄያው መልስ እንዳላገኘ ጀኖሳይድ ወች አስታውቋል።

ዶ/ር ስታንተን በደብዳቤያቸው “በተለይ ረሀብንና ምግብ መከልከልን እንደ መሳሪያ በመጠቀም የኦጋዴንን ህዝብ ለመጉዳት የሚደረገው እርምጃ በእጅጉ እንዳሳሰባቸው፣ አካባቢውን ከመከላከያ ሰራዊት በስተቀር ሌላ አካል እንዳይጎበኘው መደረጉ ትልቅ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን” ገልጸዋል።

በሴፕቴምበር 24 ቀን 2003 ዓም በመለስ ዜናዊ ቤሮ ውስጥ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አዲሱ ለገሰ፣ የህወሀት ባለስልጣን የሆነው ስብሀት ነጋ፣ የማስታወቂያ ሚኒስትር በረከት ስምኦን፣ የጋምቤላ የደህንነት ሃለፊ አሞት አባንግ አሎም፣ የፌደራል ደህንነት ሃለፊ አለማየሁ፣ የፌደራል ጉዳዮች ሀላፊ አባይ ጸሀየ፣ ኢታማጆር ሹም ሳሞራ (ሙሀመድ) የኑስ፣ የመከላከያ ሰራዊት የስለላ ሃለፊ ብርጋዴር ጄኔራል ዮሀንስ ገብረመስቀል፣ እንዲሁም የመከላከያ ሚኒስትር አባዱላ ገመዳ በጋምቤላ ያለውን የጸጥታ ሁኔታ ለመወያየት ተሰብስበው የዲሰምበር 13 ፣ ቀን 2003 ዓም ጭፍጨፋ እንዲጀመር ውሳኔ አስተላልፈዋል ሲል የጄኖሳይድ ወች ድብዳቤ ጠቅሷል።

በጄኖሳይድ ወች ምርመራ መሰረት ግድያው የተፈጸመው በጊዜው በጋምቤላ ተመድቦ በነበረው የመከላከያ ሰራዊት አዛዥ ጻጋየ በየነ ትእዛዝ ሲሆን፣ ትእዛዙን በቀጥታ ያገኘውም በወቅቱ የፌደራል ጉዳዮች ከፍተኛ ባለስልጣን ከነበረው ዶ/ር ገብረአብ በርናባስ ነበር። ታደሰ ሀይሌ የተባለው የፖሊስ አዘዥም ትእዛዝ በመስጠት መሳተፉትን ድርጅቱ ገልጿል።

የጭፍጨፋው ዋና ምክንያት አካባቢውን በነዳጅ ፍለጋ ላይ ለተሰማሩት የቻይና ኩባንያዎች ለማስረከብ ሲሆን፣ አሁን እየታየ ባለው ሁኔታ አኝዋኮችን ከቦታቸው ለማፈናቀል ሌሎች ከፍ ያሉ ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ድርጅቱ አስታውሷል።

ባለፉት ወራት አኝዋኮች የሰፈሩባቸው ቦታዎች ለቻይናውያን፣ ለህንዶችና ለጃፓኖች ለ99 አመታት ለሚቆይ የጊዜ ገደብ እጅግ አነስተኛ በሆነ ክፍያ መሰጠታቸውን የገለጻው ድርጅቱ፣ እነዚህ ስምምነቶች ሲደረጉ አኝዋኮች እንዲሳተፉ አለመደረጋቸው ብቻ ሳይሆን፣ እርምጃው መለስ ዜናዊን በአለም ላይ ካሉ ቱጃር አምባገነኖች መካከል አንዱ እንዲሆን አድርጎታል ብሎአል።

ሰዎችን ያለፍላጎታቸው በዘራቸው፣ በፖለቲካ እምነታቸው፣ በባህላቸው፣ ወይም በሀይማኖታቸው ከቦታቸው እንዲነሱ ማድረግ በአለማቀፍ የወንጀል ህግ ወይም የሮማ ድንጋጌ እየተባለ በሚጠራው ህግ አንቀጽ ሰባት መሰረት ወንጀል መሆኑን ድርጅቱ ጠቅሶ፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች አስከባሪ ኮሚሽን የራሱን ህዝቦች እያሸበረ የሚገኘውን የኢትዮጵያ መንግስት ከድርጊቱ እንዲታቀብ ለማድረግ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል ሲል ጥሪውን አሰምቷል።

ድርጅቱ በጊዜው በጭፍጨፋው ተሳትፈዋል ያላቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ያወጣ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ረዳት ኢንስፔክተር ታደሰ መሬሳ፣ ረዳት ኢንስፔክተር አክሊሉ ሰካታ፣ ረዳት ኢንስፔክተር ተሸሞ ካባ፣ ሰርጄንት ንጋቱ እንግዳ፣ ሰርጄንት አበበ ጣሰው፣ ሰርጄንት አትጉ ግርማይ ፣ ሰርጄንት ገረሙ ወርጂ፣ ኢንስፔክተር ሙሀመድ ካሳ. የቡድን መሪ ደምሴ ባልቻ፣ ፖሊስ ሽብሩ ረጋሳ፣ ፖሊስ ሙለታ ቶሎሳ፣ ፖሊስ ጌታቸው ደምሴ፣ ፖሊስ አበራ በቀለ፣ ፖሊስ አሸናፊ ታደሰ፣ የቡድን መሪ በፈቃዱ አሰፋ፣ ፖሊስ ከድር አሊ፣ ፖሊስ ከበደ እንዳለ፣ የፖሊስ አዛዥ ታደሰ ሀይለስላሴ፣ ፖሊስ ከበደ ተኪሳ፣ ፖሊስ ታደለ አየለ፣ ግርማ ሊጂ፣ ግርማ ተረፈ፣ ዱባለ ተሰማ፣ አድኖ ለገሰ፣ ገበያው አድሳ፣ አየለ ታደሰ፣ ወንድሙ ፈይሳ፣ እንዳለ ጃለታ፣ ክኔሳ ጨዋካ፣ መስካለ ዲቻ፣ ሽብሩ ሬታ፣ ኩንዳ የተባለ የፖሊስ ጤና ክፍል ሃላፊ እና መኮንን የተባለ የፖሊስ የደህንነት ሀላፊ ይገኙበታል።

## ወያኔ የአሜሪካንና የግንቦት7ን ድምጾች . . . ከገጽ 1 የዞረ

በሌላ ዜና ደግሞ የግንቦት7 ሬዲዮ በጉጂ ብሄረሰብና በአላሙዲን የወርቅ ማውጫ ኩባንያ መካከል የተፈጠረውን ችግር በተደጋጋሚ ሲዘግብ መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ሰሞኑን የወያኔ አገዛዝ ችግሩ መኖሩን ሳይወድ በግድ ከተቀበለ በሁዋላ፣ ለትምህርት ቤት ማሰሪያ በሚል ሰበብ 24 ሚሊዮን ብር ላካባቢው ህዝብ መስጠቱ ታውቋል። ችግሩን ለመደባባቅ ሙከራ ሲያደርግ የቆየው ወያኔ፣ በህዝቡ ጠንካራ ተቃውሞ ምክንያት በስተመጨረሻ ችግሩን አምኖ ለመቀበልና ባለሀብቱን ለማስገደድ እንደቻለ በቴሌቪዥን ባሰራጨው ዜና ላይ ለማወቅ ተችሎአል። የግንቦት7 ሬዲዮ የጉጂ አካባቢ ህዝብ የአላሙዲን ንብረት የሆኑ መኪኖች በአካባቢው እንዳይንቀሳቀሱ አግዶ መያዙንና በአካባቢው ስላለው አለመረጋጋት በተደጋጋሚ ሲዘግብ መቆየቱ ይታወሳል።

## እርዳታን ለፖለቲካ ስራ ማዋል የወያኔ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ቢታወቅም አሁንም ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ በመቶ ሺሆች የሚቆጠሩ የኦጋዴን ክልል ሶማሊዎች በርሃብ ማለቃቸውን ጠቅሷል።

በያዝነው ዓመት የቅርብ ወራት ደግሞ የወያኔው አገዛዝ መሪዎች አሁንም ለርሃብተኞች ርዳታ የመጣ እህልን ለፖለቲካ ፍጆታ በማዋል ተረጂዎች በግዴታ የአገዛዙ ፓርቲ አባል እንዲሆኑ ማድረጋቸውን እንዲሁም በመጪው ግንቦት ወር ለሚደረገው ምርጭ ወያኔ በስልጣን እንዲቆይ አገዛዙን ብቻ እንዲመርጡ በማስፈራሪያነት የተተቀሙበት መሆኑን መግለጫው አውስቷል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም የብሉምበርጉ ጋዜጠኛ ጃሶን ማክለር የዚህን የምግብ ርዳታ ለፖለቲክ ፍጆታ የማዋል ተግባርን በማጣራት ላይ እያለ መቀሌ ላይ ለእስር የተዳረገ መሆኑን መግለጫው አክሎ ገልጿል።

የግንቦት ሰባት እንቅስቃሴ ባወጣው በዚሁ መግለጫ ላይ በሰጠው ማጠቃለያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በርሃብ አለንጋ እየተገረፉ ባሉበት ሁኔታ ለነዚህ ችግረኞች ነፍስ መታደጊያ የሚላክ ርዳታን ለጦር መሳሪያ ግዢ ማዋል በሰው ልጆች ሰባዊ መብት ላይ የሚፈጸም ወንጀል እንደሆነ እንደሚያምን ገልጾ፣ የወያኔ መሪዎች እንዲህ አይነቱን ተግባር የሚቀጥሉ ከሆነ በማስተዋልና ባንክሮ ልናነሳው የሚገባን ዋና ጥያቄ የወያኔው አገዛዝ እንዲህ በአደባባይ የረሀብተኞችን ርዳታ በተገለጸው መልኩ ለፖለቲካዊ ፍጆታው እያዋለ ባለበት ሁኔታ የአሜሪካንና የእንግሊዝ መንግስታት የሚያደርጉትን ርዳታ ለምን አሁንም በገፍ እየቀጠሉ ይገኛሉ? የሚለው መሆን እንዳለበት በማሳሰብ የአሜሪካን፤ የእንግሊዝ፤ የጀርመንና ሌሎችም ለጋሽ ሃገራት መንግስታት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለዲሞክራሲ እንዲቆሙና ለእንዲህ አይነት አይን ያወጣ ወንጀለኛ አገዛዝም የሚያደርጉትን ድጋፍ እንዲያቆሙ በማሳሰብ መግለጫውን አጠናቋል።

የዚሁ የቢቢሲ ዜና በርካታ የሆኑ ዓለም ዓቀፍ ሚዲያዎች ትኩረትንና ሽፋንን እንዳገኘ የታወቀ ሲሆን በ1978 ዓም የርዳታ ገንዘብ ማሰባሰብ ከፍተኛውን ሚና የተጫወተው ታዋቂው ቦብ ጊልዶፍና ሌሎች ርዳታ ለጋሽ ድርጂቶች በቢቢሲ የቀረበው ሪፖርት ውሸትና መሰረት የሌለው ነው ማለታቸውን ተከትሎ በርካታ ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ የሃሳብ መስጫ ድረገጾች የበኩላቸውን አስተያየቶች በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በዚህም መሰረት ዘ ጋርዲያን በተሰኘ ድረ ገጽ ላይ ከሰፈሩ የኢትዮጵያዊያን አስተያየቶች ውስጥ ሚኒሊክ የተባሉ አስተያየት ሰጪ ቦብ ጊልዶፍ እየተጨነቀ ያለው ስለራሱ ክብር ወይስ እውነታው ስለመጋለጡ ነው ካሉ በኋላ የተለያዩ ሃገራት ተሞክሮዎችን እንደምሳሌነት ከጠቀሱና የወያኔንም ባህሪ ከዘረዘሩ በኋላ በጣም የሚያሳዝነው ነገር አሁንም ምእራባዊያን ሃገራት በመጃጃል ለመለስ ዜናዊ የሚያደርጉትን ድጋፋቸውን መቀጠላቸው ነው ብለዋል። በሌላም በኩል ግሎባል ቮይስ በተባለ ድረ ገጽ ላይ ሃብቱ የተባሉ አስተያየት ሰጪ አሁንም ቦብ ጊልዶፍ ካለፈው ስህተቱ ሳይማር ድጋሚ ስህተትን ለመስራት እየተዘጋጀ ነው ካሉ በኋላ የልቁንስ ቦብ ያለውን ሃይልና ጊዜ ተጠቅሞ ወያኔ በርግጥም በምን መልክ ገንዘቡን ለጦር መሳሪያ ግዢ እንዳዋል በምን ስልትም ምእራባዊያንን ሊያጃጂላቸው እንደቻለ ቢያጣራ ይቀለዋል ሲሉ ሃሳባቸውን አካፍለዋል።

## አሜሪካዊው ሴናተር የአሜሪካ መንግስት . . . ከገጽ 1 የዞረ

ዋነኛ ትኩረቱን በሱዳንና በኢትዮጵ ላይ ያደረገው የሴናተር ፊንጎልድ መግለጫ አያይዞም “ ኢትዮጵያ የአሜሪካ ጠቃሚ አጋር አገር ናት፣ በጋራ የምንጋራቸው በርካታ ነገሮችም አሉ። ለኢትዮጵያ በእያመቱ በብዙ መቶዎች የሚቆጠር ድጋፍ እናደርጋለን። ለዚህም ነው ጉዳዩ በጣም ያሳሰበኝና በጠንካራ ቃላት ትችቶችን እንድሰነዝር ያደረገኝ። የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ወደፊት እንጂ ወደ ሁዋላ እንዳይሄድ ሀላፊነት አለብን ብየ አስባለሁ። አሁን ምርጫው ከሶስት ወር ያላነሰ ጊዜ ቀርቶታል። ይሁን እንጅ በርካታ የተቃዋሚ ፖለቲካ መሪዎች በእስር ላይ ናቸው፤ ከእነዚህም መካከል የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ መሪ የሆኑት ወ/ት ብርቱካን በዋናነት ይጠቀሳሉ። ይህ ምርጫ እነዚህ የፖለቲካ መሪዎች ታስረው በምንም ታምር የሚታመን ሊሆን ይቀርና ፍትሀዊ እንኳን አይሆንም።” ይላል።

ሴናተሩ የአሜሪካ መንግስትና የአለማቀፉ መህበረሰብ መውሰድ ስላለበት እርምጃ ሲናገርም “ሌላው ቀርቶ የአሜሪካ መንግስትና የአለማቀፉ ማህበረሰብ እነዚህ የፖለቲካ መሪዎች ከግንቦቱ ምርጫ በፊት እንዲፈቱ ጥረት ማድረግ አለበት። ምንም የሚለወጥ ነገር ከሌለ ግን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን ለመቆም ፈጽሞ መፍራት የለብንም ብቻ ሳይሆን ለስም ተብሎ የሚደረግ ምርጫ የአገሪቱ ህዝብ ለምርጫ ምንም አይነት ፍላጎት እና እምነት እንዳይኖረው የሚያደርግ እርምጃ መሆኑን በግለጽ ቋንቋ መናገር መቻል አለብን።” ሲሉ አቋማቸውን ይፋ አድርገዋል።

ሴናተር ፊንጎልድ በኢትዮጵያ፣ በሱዳን፣ ዩጋንዳ፣ ሩዋንዳና ቡሩንዲ ላይ ያወጡት ጠንካራ መግለጫ የኦባማ አስተዳደር በውስጥ ጉዳዮች ላይ ተወጥሮ ችላ ብሎት የቆየውን የአፍሪካ ፖሊሲ እንዲፈትሽ የሚያሳስብና የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ባህሪ ገሀድ ያወጣ መሆኑን ታዋቂው የፖለቲካል ሳይንስና የህግ ምሁር የሆኑት ፕሮፌሰር አልማርያም ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን የሚታየው የሰብአዊ መብት ጥሰት ነጻ ምርጫ ለማድረግ አያመችም በሚል የካርተር ማእከል ታዛቢዎችን ወደ ኢትዮጵያ እንደማይልክ ማስታወቁ ይታወሳል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661